# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2015/01*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

---

**የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በግብርና-ተኮር ንግድ ፈር-ቀዳጅ ለሆኑ ሴቶች ዕውቅና ሰጠ**

*የግብርና-ተኮር ንግድ የሴት አመራሮች ትስስር በግብርናው ዘርፍ የተሠማሩ የሴት ሥራ ፈጣሪዎችን ዕድገትና ፈጠራ አደነቀ*

***አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤ጥር 13 ቀን 2007 ዓ.ም.፡-*** በግብርናው መስክ በንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሴቶችን ቀጣይነት ባለው መልኩ ለማብቃትና በዘርፉ የፆታ እኩልነትን ለማስፈን፤ የአሜሪካ መንግሥት በዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲው በኩል በግብርና-ተኮር ንግድ ላይ የተሠማሩ የሴት አመራሮች ትስስር 100 አባላትን አስመረቀ ፡፡ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክና የኢትዮጵያ ቀዳማዊት አመቤት ወ/ሮ ሮማን ተስፋዬ የምረቃ ሥነ ሥርዓቱን በጋራ በመክፈት ተመራቂዎቹ በንግድ ሥራ ፈጠራ በግብርናው መስክ ያለውን የንግድ ሥራ ለማሻሻል ያደረጉትን አስተዋጽኦ አድንቀዋል፡፡

በኢትዮጵያ በግብርናው መስክ ከተሠማሩ ዜጎች ገሚሱ ሴቶች ሲሆኑ፤ለቤተሰብ ፍጆታ በሚውለውም ሆነ ለገበያ በሚቀርበው ምርት በማምረት ሂደት ውስጥ የጎላ ሚና አላቸው፡፡ ይሁንና ምን ዓይነት ሰብሎች ይዘሩ አልያም መቼ ለገበያ ይቅረቡ በሚለው የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ አይደሉም፡፡ በአጠቃላይ ለሥልጠና፣ለገበያ መረጃ፣ለግብይትና ለብድር አገልግሎቶች ያላቸውን ውስን ተደራሽነት በግብርናው መስክ ባለው የንግድ ሥራ ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን አድርጓል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ በግብርና ምርት ገበያ ልማት መርሀ ግብሩ በኩል በግብርናው መስክ በንግድ ሥራ ላይ የተሠማሩ ሴት አመራሮች ትስስርን በግንቦት ወር 2006 ዓ.ም. የከፈተ ሲሆን፤ዓላማውም ለአባላቱ የንግድ ሥራዎቻቸውን በሚገባ ማቀድና መቆጣጠር ይችሉ ዘንድ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡ በብድርና ቁጠባ ዙሪያም አስፈላጊውን መረጃ የግብርና-ተኮር ንግድ የሴት አመራሮች ትስስር ያቀርባል፡፡ ከአዲስ አበባ፣አማራ፣ኦሮሚያ፣ደቡብና ትግራይ ክልሎች የተውጣጡ 100 ሴት አመራሮች በግብርና-ተኮር ንግድ አመራር፣ በንግድ ሥራ ክትትልና ትስስር ሥልጠና ወስደዋል፡፡ **እነዚህ በዘርፉ የተሠማሩና በትስስሩ የታቀፉ አርአያ ሴት የንግድ ባለሙያዎች በተለያየ ደረጃ በግብርናው መስክ የንግድ ድርጅቶች ባለቤቶችና አንቀሳቃሾች ሲሆኑ፤ማምረትን፣ማቀነባበርን፣መሸቀጥንና ለውጭ ገበያ መላክን ጨምሮ በተለያየ መልኩ የሚሳተፉ ናቸው፡፡**

አምባሳደር ፓትሪሺያ ሃስላክ በሥነሥርዓቱ ላይ ሲናገሩ፡- "አብዛኞቻችሁ ወንዶች በበላይነት በሚቆጣጠሩት እንደ ቡና፣ሰሊጥና በቆሎ የመሳሰሉ የግብርና ምርቶችን ለውጭ ገበያ የምታቀርቡ ቆራጥ ነጋዴዎችና ላኪዎች ናችሁ" ብለዋል፡፡ አክለውም፡- "ዛሬ በዚህ በንግድ ሥራ አመራር መርሀ ግብር በመሳተፋችሁ ከፍተኛ አድናቆት ሊቸራችሁ ይገባል" ሲሉ ያላቸውን አድናቆት ገልፀዋል፡፡

በምረቃ ሥነሥርዓቱ ወቅት፣ አምስት የንግድ ሥራ ፈጣሪ ሴቶች አዳዲስ ሥራዎችን የሚጀምሩበትና ነባር እንቅስቃሴዎቻቸውን የሚያስፋፉበት ሽልማት አሸናፊ ሆነዋል፡፡ በተጨማሪም የአሜሪካ ዓለም

አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ሴቶችን በአባልነት በመመልመልና በማበረታታት ስኬታማ ለሆኑ 17 የገበሬ ማኅበራት ያለውን አድናቆት ገልጿል። ኤጀንሲው ካለፈው ዓመት መጋቢት ወር ጀምሮ እስከ ታኅሣሥ ወር 2007 ዓ.ም. ድረስ ከአራቱ ክልሎች ለ1700 ያህል የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት ትራክተሮችንና ሞተር ብስክሌቶችን እንዲሁም ከ5400 በላይ ሴት አባላትን ላስመዘገበ አንድ ማኅበር በዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒት ላይ ለመሳተፍ ዕድል ለማመቻቸት ቃል ገብቷል።

በአሜሪካ አለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ የሚመራው የግብርና ምርት የገበያ አቅርቦት ማሳደጊያ ፕሮግራም በኢትዮጵያ የሚተገበረው መጪውን ትውልድ መመገብ (Feed the Future Initiative) የተሰኘ መርሀ ግብር ዋና አካል ሲሆን የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ለኢትዮጵያ መንግሥት የግብርና ዕድገት መርሀ ግብር ከሚያደርገው ድጋፍ ትልቁን ድርሻ የሚይዝ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ረሃብን ለማጥፋትና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በአሜሪካ መንግሥት የተመደበው 3.5 ቢሊዮን ዶላር፤የአሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያ ዋነኛ አጋር በመሆን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ መሠረት የሆነውን የግብርናውን ዘርፍ ለማሳደግ ከፍተኛ እገዛ በማድረግ ላይ ይገኛል።

###

###